ማህረሰቡን፣ ይህ ክፍል ቸላ ቢለን በያለንበት በሃገርም ውስጥም ሆነ በውጭ በሰላማዊ
ሰልፍችም ሆነ በሌሎች ዘዴያች ህዝብን እየቀሰቀስን የተጣመሙ አስተሳሰቦችን ለማቅናት
የህግ የበላይነት ተበሏልና ህግና ፍትህ ኃይልን እንዲሸሩ፣ ዲሞክራሲ ተበሏልና በአን
ዳንድ ኃያላን ትብብር በሃገራችን የተተከለው አፋኝ አገዛዝ እንዲወገድ፣ ሰብአዊ መብ
ት ለሰብአዊ ፍጡሮች በሙሉ ተበሏልና የኢትዮጵያውያንም መብቶች እንዲከበሩ፣ የመላ ዓ
ለም ህዝቦች የጋራ ህልም የሆነው የሰላም ጸጋ የኛም ህልም ነውና ኃያላን መንግሥታት
አመጽንና አብሪትን ከሚያግዙ አቋሞችና ድርጊቶች ተቆጥበው በፍትህና በህግ ለተመሠረተ
ሰላም ጸንተው እንዲቆሙ እየጠየቅን መንቀሳቀስ እንችላለን::

ከዚህ አንጻር ሲታይ ኢተፖዶህ ለዓለም አቀፉ ኮሙኒቲ ያደረገው ጥሪ ወቅታዊ የ
ሆነውን ያህል በውጭም በውስጥም ለሚገኙ ኢትዮጵያውያንም በዚህም በዲፕሎማሲው መስክ በ
አዲስ ኃይልና በአዲስ መንፈስ የኢትዮጵያን፣ የህግ የበላይነትን፣ የፍትህን ድምጽ በህ
ዝባችን ስም ለውጭው ዓለም እናስተጋባ የሚለም ሃገራዊ ጥሪ ስለሆነ ኢትዮጵያውያን በሙ
ሉ በያሉበት ተንቀሳቅሰው ተጨባጭና አወንታዊ መልስ እንዲሰጡ ይጠበቅባቸዋል::

[signature]
09/07/99